# የአባላዘር ተላላፊ በሽታዎች እውነት ነገሮች



## የአባላዘር ተላላፊ በሽታዎች ፍሬ ነገር

### የበሽታ ምልክቶች

የሚከተሉት ምልክቶች ካሉ ለሃኪም ይንገሩ

*ሴቶች፥*

- ያልተለመደ ፈሳሽ ወይም ሽታ ከብልት
- ብልት አካባቢ ማሳከክ ወይም ማቃጠል
- የወር አበባ አለ ግዜው መምጣት
- በግንኙነት የማህጸን ማመም
- የማያቋርጥ፥ ምክንያት የሌለው፡ የማህጸን ማመም

*ወንዶች፥*

- መግል ወይም ሌላ ፈሻሽ ከብልት

*ሁለቱ፥ ወንድና ሴት፥*

- መጥፎ ቁስል ወይም እባጭ በብልት፥ አፍና ፊንጢጣ አካባቢ
- ሲሸኑ ወይም በሰገራ ግዜ ማቃጠልና ማመም
- ኢንፍሉወንዛ የሚመስል ትኩሳትና የአካል ምሉ ማመም
- በብልት አካባቢ ማበጥ

### የሚከተሉትን ነገሮች አይርሱ፥

- አብዛኞቹ የአባላዘር በሽታዎች ምልክት የላቸውም
- አንዳንድ ግዜ ምልክተቹ ብዜዱም በሽታው ይኖራል
- አንዳንድ ሰዎች ለተለመደ የሕክምና ምርመራ ደም ሲሰጡ የአባላዘሩን በሽታ አንድላይ የሚመረመር ይመስላቸዋል፤ነገር ግን አይደለም። የበሽታ ጥርጣሬ ካለዎት ለሃኪም ነግረው በደንብ ይመርመሩ።
- የአባላዘር በሽታዎች በተለመደ የሴቶች የማህጸን ምርመራ ሊገኙ አይችሉም። ወንዶችና ሴቶች በአባላዘር በሽታ አደጋ ላይ ካሉ ለሃኪማቸው መንገር አለባቸው።

### መተላለፍ

አብዛኖቹ የአባላዘር በሽታዎች የሚተላለፉት፥

- በእምስ ግብረስጋ ግንኙነት
- በአፍ ግብረስጋ ግንኙነት
- በፊንጢጣ ግብረስጋ ግንኙነት
- የሱስ መድሃኒት ለመውሰድና ለንቅሳት መርፌ ሲካፈሉ
- ከታመመች እናት አዲስ ወደተወለደ ህጻን

### ጣጣውና የሚያስከትለው ችግር

ሳይታከሙ ከቀሩ፥ አንዳንድ የአባላዘር በሽታዎች፥

- በጣም አስጊና አሳማሚ ሊሆኑ ይችላሉ
- የመውለድ አካሎችን ያበላሻሉ
- በወንዶችና ሴቶች መሃንነት ያስከትላሉ
- በሽታው፥ ወደ ግብረስጋና መርፌ ተካፋዮች፥ ያስተላልፋሉ
- አዲስ ወደተወለዱት ሊተላለፍ፥ በጣም አስጊ ችግርና፥ እስከ ህጻናት ሞት ሊያስከትል ይችላል።
- የልብ በሽታ፥ ዕውርነት፥ ቁርጡማት፥ የአንጎል ብልሽትና ሞት ያስከትላል።

### መከላከል

የአባላዘር በሽታዎች እንዳይዛመቱ የሚረዱ አስተያየቶች፥

- የሴት ብልት፥ የአፍና ፊንጢጣ ግብረስጋ ማቆም ከሁሉም የበለጠ መከላከያ ነው።
- ላቴክስ ኮንዶን ሁሎግዜና በትክክል ከተጠቀሙባቸው ኤይድስ የሚያስከትለውን የኤች-አይ-ቪ ቫይረስን ለመከላከል ይችላሉ። በተጨማሪም የአባላዘር በሽታዎችንም ሊከላከሉ ይችላሉ።
- የላቴክስ ኮንዶም መከላከያ በተደረገላቸው የብልት ቁስልና የኤች-ፒ-ቪ በሽታ፥ በብልቶች አካባቢ ሊያስከትል ይችላል። ባልተሸፈኑትና መከላከያ የሌላቸው ቦታዎችንም ሊወጡ ይችላሉ። የላተክስ ኮንዶም ሁሉግዜና በደንብ ከተጠቀሙባቸው የብልት ሄርፒስ፥ ቂጥኝ፥ ከርክርና የኤች-ፒ-ቪ በሽታን ሊቀንሱ ይችላሉ። በተጨማሪም፥ የላተክስ ኮንዶሞች ከኤች-ፒ-ቪ የሚነሱትን የማህጸን በሽታዎችን መባዛት ይቀንሳሉ።
- የወንድ ብልትና አፍ ግብረስጋ ስያደርጉ ኮንዶም ይጠቀሙ
- የአፍና የሴት ብልት ግንኙነት ሲያደርጉ የላተክስ ኮንዶም መከላከያ ያድርጉ
- ተካፋይዎ፥ እሱ ወይም እሷ፥ የአባላዘር በሽታ የለብንም ቢሉም፥ ሁሉግዜ ኮንዶም ይጠቀሙ።
- የአባላዘር በሽታ ከሚጠረጠር ግብረስጋ አያድርጉ
- የግብረስጋ ተካፋዮችዎ ይቀንሱ
- የበሽታው ጥርጣሬ ካለዎት ሃኪም ወይም ሌላ የህክምና ድርጅት በመሄድ ይመርመሩ
- ከታመሙ ተካፋዮችዎን ያስታውቁ
- ተካፋዮችዎ እንዲመረመሩና እንዲታከሙ ይምከሩ
- ባመት ሁለት ግዜ፥ ፊንጢጣም ጭምር፥ ይመርመሩ
- የወንድ ኮንዶም ከሌለ፥ እምስ ውስጥ የሚገባ የሴት ኮንዶም ጥሩ መፍትሄ ነው።

### ሕክምና

የአባላዘር በሽታ፥ ምናልባት፥ ካለዎት፥

- የአባላዘር በሽታን የሚጠራጠሩ ከሆነ፥ ሃኪም ወይም ሌላ የሕክምና አገልግሎት ሂደው ይመርመሩ
- አብዛኞቹ የአባላዘር በሽታዎች በአንቲባዮቲክ (ፐንስሊን) ሊድኑ ስለሚችሉ፥ ሕክምና ይውሰዱ
- በቤት ውስጥ ራስዎን አያክሙ


ለተጨማሪ ማብራርያ በሚከተለው ይጠይቁ፥

Infectious Disease Epidemiology, Prevention and Control Division
Minnesota Department of Health
P.O. Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
(651) 201-5414; (651) 201-5797 TTY

Minnesota Family Planning and STD Hotline
1-800-783-2287 ድምጽ /TTY

CDC National STD and AIDS Hotlines
1-800-227-8922; 1-800-243-7889 TTY


በ Minnesota Department of Health, STD and HIV Section የተዘጋጀ - ጥር 2002 rev 2006